# ፀሀይን መመልከቻ መሳሪያ:
## የአጠቃቀም መመሪያዎች






**ሙሉ የፀሀይ ግርዶሽ**

*ሰኞ ፣21አገስት2017*

© 2014-2017
Eclipse2017.org, inc.

# TERMS AND CONDITIONS FOR USE OF SOLAR VIEWER

**Please read these Instructions for Use carefully before using the Solar Viewer. Your purchase and use of the Solar Viewer constitutes your agreement to these terms and conditions. Failure to follow these Instructions for Use may result in serious personal injury, including permanent eye damage. If you do not understand these Instructions or cannot follow them diligently and completely, then you should not look at the Sun at any time, with or without a Solar Viewer.**

The term “Solar Viewer” refers to the special cardboard-and-polymer optical products, marked “SAFE FOR DIRECT SOLAR VIEWING”, manufactured by Rainbow Symphony of Reseda CA, and sold by Eclipse2017.org for the purpose of viewing the Sun during the solar eclipse of August 21, 2017, by or under the direct supervision of a person 18 years of age or above and in accordance with these Instructions for Use.

Observing the Sun directly, without the benefit of eye protection provided by the Solar Viewer, will likely result in serious personal injury, up to and including permanent eye damage and blindness. When these Instructions for Use are followed completely and precisely, the undamaged and unmodified Solar Viewer has been proven to be safe and effective in allowing direct, short-term, viewing of the Sun. If these Instructions for Use are not followed, or if damaged or modified Solar Viewers are used, permanent eye injury could result.

You should never look directly at the Sun, with or without the aid of the Solar Viewer, if you have any temporary or permanent medical or other condition which either (1) prevents your use of the Solar Viewer according to these Instructions for Use, or (2) which predisposes you to an increased or special risk of incurring, worsening, or contributing to the effects of any optical or other medical, health, or other condition, by looking or attempting to look at the Sun.

You should never attempt to perform any other activity (such as driving or walking) while using the Solar Viewer.

You agree that if you let others use the Solar Viewer, you will provide each such user with a copy of these Instructions for Use and will make sure such user reads and understands the Instructions for Use before using the Solar Viewer.

By using the Solar Viewer to view the Sun, you agree with the following:

(a) you understand these Instructions for Use completely;
(b) you understand and accept the risks associated with improper use of the Solar Viewer;
(c) you accept full responsibility for, and assume all risks associated with, the act of viewing the Sun, with or without the use of the Solar Viewer; and
(d) the Solar Viewer is fragile and any damage to it or modification of it will render it immediately and permanently unusable for its intended purpose.

## Release and Limitation of Liability

By way of purchasing and using the Solar Viewer, you are irrevocably releasing, indemnifying, and holding harmless the manufacturer and seller from any liability, loss, claim and expense (including attorney’s fees), including but not limited to bodily injury or other personal harm, which may result from using the Solar Viewer under any circumstances or conditions and irrespective of jurisdiction. Neither the manufacturer nor the seller will be responsible for any damages of any kind, irrespective of reasons, conditions or circumstances, including malfunctioning of the Solar Viewer. All risks associated with using the Solar Viewer rest solely and entirely with the user, irrespective of whether the Solar Viewer is used by the original purchaser or any third party. You fully understand and assume the risks in using the Solar Viewer. You confirm that you have read this release of liability and fully understand its terms and that you have given up substantial rights by purchasing and using the Solar Viewer.

THE MANUFACTURER AND SELLER OF THE SOLAR VIEWER MAKE NO WARRANTY OF ANY KIND, EXPRESSED OR IMPLIED, WITH RESPECT TO THE SOLAR VIEWER, INCLUDING BUT NOT LIMITED TO THE IMPLIED WARRANTIES OF MERCHANTABILITY, FITNESS FOR A PARTICULAR PURPOSE, AND NON-INFRINGMENT. NEITHER THE MANUFACTURER NOR THE SELLER SHALL BE LIABLE FOR ANY OTHER DAMAGES, INCLUDING BUT NOT LIMITED TO DIRECT, INDIRECT, INCIDENTAL, SPECIAL, CONSEQUENTIAL, OR EXEMPLARY DAMAGES, WHETHER IN AN ACTION IN CONTRACT OR TORT (INCLUDING NEGLIGENCE AND STRICT LIABILITY), SUCH AS, BUT NOT LIMITED TO, LOSS OF ANTICIPATED PROFITS OR BENEFITS RESULTING FROM, OR ARISING OUT OF, OR IN CONNECTION WITH THE USE OR FURNISHING OF THE SOLAR VIEWER OR THE PERFORMANCE, USE OR INABILITY TO USE THE SAME, EVEN IF THE MANUFACTURER OR SELLER HAS BEEN ADVISED OF THE POSSIBILITY OF SUCH DAMAGES. IN NO EVENT WILL THE MANUFACTURER’S OR SELLER’S TOTAL LIABILITY EXCEED THE PRICE PAID FOR THE PRODUCT.

## Note Regarding Translations

Translations of these Instructions for Use into various languages are provided “AS-IS” and solely for the convenience of the reader. Eclipse2017.org has made reasonable efforts to ensure the accuracy of the Translations; however, in the event of any perceived discrepancy in meaning or interpretation between the English version and any Translation, the English version will prevail. You should not act in reliance on anything contained in any Translation of these Instructions for Use, but should refer to the official English version.


*© 2016-2017*
*Eclipse2017.org, inc.*


# *ሙሉ የፀሀይ ግርዶሽ - 21 ኦገስት 2017*

**ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንኳን ደህና መጡ!**

የፀሀይን ሙሉ ግርዶሽ ለመመልከት ሀገራችንን ለመጎብኘት ስለ ወሰኑ ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል፣እና ሁሉም ሰዉ ይህን አስደናቂ ክስተት ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እንዲመለከት እንፈልጋለን!

*እነዚህን መመሪያዎች በአማርኛ ቋንቋ ያቀረብነዉ ለእርስዎ ምቾት በማሰብ ነዉ፡፡ የእነዚህ መመሪያዎች፣አጠቃቀሞች እና ማሳሰቢያዎች ("መመሪያዎች") የእንግሊዝኛ ትርጌሜ፣የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን በመጠቀም ፀሀይን በተገቢዉ እና በትክክለኛ መንገድ ለመመልከት የሚያስችል የተሟላ መረጃ እና መመሪያ ነዉ፡፡ መመመሪያዎቹ በ http://tinyurl.com/viewer-instructions ይገኛሉ፣እና የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ለመጠቀም እርስዎ መመሪያዎቹን ማንበብ፣መረዳት እና መከተልዎ አስፈላጊ ነዉ፡፡**መመሪያዎቹን ሳይከተሉ መቅረት እርስዎ ላይ አሳሳቢ የሆነ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡***

በ ኦገስት 21, 2017 የሚከሰተዉን የፀሀይ ግርዶሽ አስትሮኖመሮች "ሙሉ የፀሀይ ግርዶሽ" ብለዉ ይጠሩታል፣ነገር ግን እርስዎ ምሉዕነቱን ለመመልከት እንዲችሉ፣USA(ዩኤስኤ) በሚያቋርጥ በጣም ቀጭን የሆነ የመሬት ክፍል("የምልዑነት አቅጣጫ" ተብሎ የሚጠራዉ) ዉስጥ መገኘትዎ አስፈላጊ ነዉ፡፡እርስዎ በዚህ አቅጣጫ ዉስጥ ካልተገኙ፣እርስዎ ከፊል የፀሀይ ግርዶሽን ብቻ የሚያዩ ይሆናል! ስለሆነም እርስዎ በምልዑነት አቅጣጫዉ ዉስጥ መገኘት ወይም አለመገኘትዎን ለይቶ ማወቅዎ እጅግ አስፈላጊ ነዉ፣እና እርስዎ ሊጠቀሙ የሚገባዎት አካሄዶች በአጭሩ ይብራራሉ፡፡



*የምሉዕነት አቅጣጫ*

## [የፈጣን አጀማመር አመልካች]   [ዝርዝር መመሪያዎች]

"የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያ" የሚለዉ ሀረግ፣በዚህ መመሪያ ዉስጥ እንደተጠቀሰዉ፣ በመጀመሪያዉ ገጽ ላይ የሚገኘዉ ማሳሰቢያዎች ዉስጥ የተቀመጠዉ እና ከዚህ በኋላ በዚህ መመሪያ ዉስጥ የትኛዉም ቦታ ላይ የተጠቀሰዉን "Solar Viewer" ይወክላል፡፡

እርስዎ ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ ህጋዊ የሆነ ስምምነትን ያካትታል፡፡በየትኛዉም ጊዜ በፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉ ፀሀይን ለመመልከት በመመሪያዉ ዉስጥ የሚገኙትን ሁሉንም መመሪያዎች እና አጠቃቀሞች ትክክለኛ እና በተሟላ መልኩ መከተልዎ አስፈላጊ ነዉ፡፡መመሪያዎቹን መረዳት ካልቻሉ፣ወይም መመሪያዎቹን በተሟላ እና ትክክለኛ በሆነ መልኩ መከተል ካልቻሉ፣ወይም የቀረቡትን ማሳሰቢያዎች ለመቀበል ካልተስማሙ፤በየትኛዉ ጊዜ፣የትኛዉንም አካሄድ ተከትለዉ ፀሀይን ለመመልከት እንዳይሞክሩ ማስጠንቀቂያ እና ምክር ይሰጦታል፡፡

*© 2014-2017*
*Eclipse2017.org, inc.*

# *የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያ የፈጣን አጀማመር አመልካች*

*ይህ ፈጣን አጀማመር የፀሀይ ግርዶሽን ለመመልከት እንዲችሉ እርስዎ በጥልቀት ሊያነቡት፣ሊገነዘቡት እና ሊተገብሩት ከሚገባ ከ [አማርኛ ዝርዝር መመሪያዎች](#) የተጨመቀ መረጃ ነዉ፡፡*

1) እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ የሚሆን ወይም የማይሆን መሆኑን ለማወቅ እና በተጨማሪም በአካባቢዉ ከፊል እና (የሚሆን ከሆነ) ሙሉ ደረጃ የፀሀይ ግርዶሽ የሚከሰትበትን ግምታዊ ሰዓቶች ለማወቅ፣ እርስዎ የሚገኙበትን አካባቢ ከ http://tinyurl.com/find-times ላይ ይመልከቱ፡፡

2) ሙሉ የፀሀይ ግርዶሽ እጅግ አስደናቂ ክስተት ነዉ፣ ነገር ግን የምልዑነትን ክስተት ሊመለከቱ የሚችሉት እርስዎ "በምልዑነት አቅጣጫ" ዉስጥ ከተገኙ ብቻ ነዉ – ይህ አቅጣጫ ደግሞ ስፋቱ የተወሰነ መቶ ማይሎች ብቻ ነዉ፡፡ እርስዎ መጀመሪያ ካቀዱት የመመልከቻ አካባቢ ምልዑነቱ የሚታይ ካልሆነ፣ ምልዑነት አቅጣጫዉ ዉስጥ ወደሚገኝ አካባቢ እንዲሄዱ አጥብቀን እንመክርዎታለን!

3) የፀሀይ ግርዶሽን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀም ሲፈልጉ፣የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን የመስታወት ክፍል በአይንዎቾ ላይ ያድርጉት፣ይህም አይንዎቾ ፀሀይን በቀጥታ ከመመልከት ሙሉ በሙሉ ከለላ እስኪያገኙ ድረሰ ማለት ነዉ፡፡

4) ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መቼ መጠቀም ያስፈልጋል:

   ሀ. እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ ካልሆነ ፣ ፀሀይን ለመመልከት በየትኛዉም ጊዜ የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተገቢ የሆነ መከላከያ ሳይጠቀሙ ወደ ፀሀይ የሚመለከቱ ከሆነ አይንዎት ላይ ዘላቂ የሆነ ጉዳት ሊደርስቦት ይችላል!

   ለ. እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ የሚሆን ከሆነ ፣የትኛዉም የፀሀይ ብሩህ ክፍል - ምንም ያህል አናሳ ቢሆን - የሚታይ ከሆነ ፀሀይን ለመመልከት በየትኛዉም ጊዜ የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡እነዚህን መመሪያዎች መተግበር የማይችሉ ከሆነ አይንዎት ላይ ዘላቂ የሆነ ጉዳት ሊደርስቦት ይችላል!

   i. ሆኖም ግን፣ ከፀሀይ ብሩህ ክብ የትኛዉም ክፍል በማይታይበት ወቅት፣ ምሉዕነት በሚከሰትበት አጭር የጊዜ ቆይታ ብቻ ፣ የፀሀይ ግርዶሹን የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ሳይጠቀሙ መመልከት ይችላሉ፡፡

   ii. እዉነታዉን ለመናገር፣እርስዎ በምሉዕነት ወቅት ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያን የሚጠቀሙ ከሆነ፣ምንም ነገር አይታይዎትም!

   iii. ምሉዕነት ልክ እንደ አበቃ እና የፀሀይ በሩህ ክብ ወደ እይታ በሚመለስበት ጊዜ የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን በድጋሚ መጠቀም መጀመርዎ አስፈላጊ ነዉ፡፡

5) በሌላ አባባል፣

**የፀሀይ ብሩህ ክብ የትኛዉም ክፍል በሚታይበት ወቅት፣ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ አስፈላጊ ነዉ!**

*© 2014-2017*
*Eclipse2017.org, inc.*

# *ፀሀይን መመልከቻ መሳሪያ አጠቃቀም ዝርዝር መመሪያዎች*

በመጀመሪያ፣እርስዎ ሊገነዘቡዎቸዉ የሚገቡ የተወሰኑ የቃላት አጠቃቀሞች ይገኛሉ!

ለእያንዳንዱ የፀሀይ ግርዶሽ፣እና ለእያንዳንዱ በምድር ላይ ለሚገኝ አካባቢ፣የተወሰኑ ወሳኝ ክስተቶች ለሚከሰቱባቸዉ ሰዓቶች የተሰጡ ስያሜዎች ይገኛሉ፡፡ ስያሜያቸዉም እንደሚከተለዉ ነዉ:

| *የክስተቶቹ ስያሜ* | *የክስተቶቹ መግለጫዎች* | *ምን አይነት መልክ አለዉ* (ለሙሉ የፀሀይ ግርዶሽ) | *ምን አይነት መልክ አለዉ* (ለከፊል የፀሀይ ግርዶሽ) |
|---|---|---|---|
| **ሲ1** | **የከፊል ደረጃ የሚጀምርበት** |  |  |
| **ሲ2** | **ምሉዕነት የሚጀመርበት** |  | ** አይከሰትም! ** |
| ***መካከለኛ-የፀሀይ ግርዶሽ*** | **የፀሀይ ግርዶሹ-መካከለኛ ነጥብ** |  |  |
| **ሲ3** | **ምሉዕነቱ የሚያበቃበት** |  | ** አይከሰትም!** |
| **ሲ4** | **የከፊል ደረጃ የሚያበቃበት** |  |  |

## *1) ፀሀይን መመልከቻ መሳሪያ አጠቃቀም አጠቃላይ መመሪያዎች*



1) [ከተቻለ] የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ከመሸፈኛዉ በጥንቃቄ ያዉጡት፡፡

2) የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን በማይጠቀሙበት ወቅት ጉዳት የማይደርስበት ቦታ ላይ ያስቀምጡት፡፡

3) የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ከመጠቀምዎት በፊት ሁልጊዜ ይፈትሹት፣የመስታወት ፊልሞቹ በምንም አይነት መልኩ ጉዳት የደረሰባቸዉ ወይም እጥፋት ያጋጠማቸዉ ከሆነ፣ የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ወደ ላይ ይቁረጡት እና ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያድርጉት፣ እና ብልሽት ያልደረሰበት ቅያሬ ያግኙ

4) የመስታወት ፊልሞቹ በምንም አይነት መልኩ ጉዳት ከደረሰባቸዉ፣በየትኛዉም ጊዜ ቢሆን ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን አይጠቀሙ፡፡

5) የፀሀይ መመልከቻ መሳሪዉን የመስታወት ፊልም ክፍል አያዉጡት፣እና በየትኛዉም መልኩ ፀሀይን ለመመልከት ከመሳሪያዉ ዋናዉ አካል የወጣ የመስታወት ፊልም አይጠቀሙ፡፡

6) በአግባቡ-የተገጠመ፣ጉዳት ያልደረሰባቸዉ የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያ መስታወቶች እይታ ዉስጥ የሚገባ ብርሀን አደገኛ ደረጃዎችን፣ከዚህም በተጨማሪ አደገኛ ዩቪ እና ሌሎች የፀሀይ ጨረሮችን ደህንነቶን በሚጠበቅ መልኩ ይከላከላሉ፡፡ ስለሆነም በእነዚህ መመሪያዎች በቀረበዉ አቅጣጫ መሰረት፣በየትኛዉም ጊዜ ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያን መጠቀም ምንም አይነት ጉዳት አያደርስም፡፡ የፀሀይ ግርዶሽ በሚከሰትበት ወቅት ፀሀይን መመልከት የበለጠ ወይም ያነሰ አደጋ እንዲኖረዉ የሚያደርጉ ምንም አይነት የተለየ ባህሪ ያላቸዉ "የፀሀይ ግርዶሽ ጨረሮች" የሉም፡፡

7) **የፀሀይ ብሩህ ክብ የትኛዉም ክፍል በሚታይበት ወቅት ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ሲጠቀሙ፣ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሰዉ አካሄድ መሰረት መሆን አለበት፡፡ ይህ ደግሞ እርስዎ ከየትኛዉም ምንጭ በመዘገቡዎቸዉ የፀሀይ ግርዶሽ መከሰቻ ሰዓቶች ላይ አይመረኮዝም(ለመጥቀስ፣ከላይ የተጠቀሱት "ሲ2" እና "ሲ3")፡፡**

8) የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ከቴሌስኮፕ፣ከባይኖኩላር፣ከካሜራ፣ከሌንስ፣ከመስታወት፣ወይም ሌላ መስታወት ከሚጠቀም መሳሪያ፣መተግበሪያ ወይም ብርሀንን ከሚያስተላልፍ ወይም ከሚያንጸባር እቃ("መስታወት የሚጠቀም መሳሪያ") ጋር በማጣመር አይጠቀሙ፡፡

9) ይህን መሰል ምንም አይነት መስታወት የሚጠቀም መሳሪያን በፀሀይ አቅጣጫ ወይም ወደ ፀሀይ አያመላክቱ፣እና ወደ ፀሀይ በሚያመላከት፣ወይም በየትኛዉም መልኩ የፀሀይን ብርሀን በሚሰበስብ፣ትኩረት በሚፈጥር፣ወይም አቅጣጫ በሚያስቀይር ምንም አይነት መስታወት የሚጠቀም መሳሪያን በመጠቀም የፀሀይን ምስል እይመልከቱ፡፡

10) የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉ በእንስሳዎች ጥቅም ላይ እንዳይዉለ፣ወይም በጊዜያዊነት ማየት ስለተሳናቸዉ፣ማንበብ ባለመቻላቸዉ ምክንያት መሳሪያዉን ደህንነታቸዉ በተጠበቀ መልኩ ለመጠቀም የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ለመረዳት እና ለመተግበር፣ወይም ድርጊታቸዉ ሊያስከትል የሚችለዉን ጉዳት ህጋዊ በሆነ መልኩ ሀላፊነት ለመዉሰድ የማይችሉ ማንኛዉም ሰዉ ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያድርጉ፡፡

11) የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ለመጠቀም:

የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ሙሉ በሙሉ በአይንዎቾ እና በፀሀይ መካከል ይያዙ፣የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን የመስታወት ክፍል በየትኛዉም ወቅት ሙሉ በሙሉ በአይንዎት እና በፀሀይ መካከል በማድረግ ጉዳት ባልደረሰበት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያ መስታወት በኩል ወደ ፀሀይ ይመልከቱ፡፡የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉ ከካርቶን የተሰራ መነጽር ቅርጽ ሲኖረዉ፣የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ልክ እንደ መደበኛ መነጽር ለመጠቀም ካርቶኑን ማጠፍ ይችላሉ፡፡ ሙሉ የፀሀይ ግርዶሽ በማይኖርበት ወቅት(ይህም፣ከዚህ በታች በቀረበዉ ቻርት ላይ ሊረዱት እንደሚችሉት በ ሲ2 እና ሲ3 ሰዓቶች መካከል፣ማለትም እነዚህ ሰዓቶች እርስዎ ለሚገኙበት አካባቢ የሚገኙ ከሆነ)፣እርስዎ የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያ ጉዳት ያልደረሰበት መስታወት ክፍል በኩል እየተመለከቱ ካልሆነ በቀር ፀሀይን ያለ መሳሪያ አይመልከቱ፡፡



12) ፀሀይን ለመመልከት በሚሞክሩበት ወቅት አይንዎትን ከጨረር ለመከላከል፣በፋብሪካ ሲመረቱ ከማቀፊያቸዉ ዉስጥ የተቀመጡ የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያ መስታወቶች በስተቀር ምንም አይነት ሌላ ቁስ ወይም እቃ አይጠቀሙ፡፡

13) እነዚህን መመሪያዎች የሚመለከት ምንም አይነት ጥያቄዎች ካልዎት፣እባክዎትን Eclipse2017.org ን ቀጥሎ በቀረበዉ ሊንክ ያግኙ፡፡ http://tinyurl.com/viewer-questions.

*© 2014-2017*
*Eclipse2017.org, inc.*

## *2) እርስዎ ለሚገኙበት አካባቢ የተለዩ የፀሀይ ግርዶሽ ሰዓቶችን ይወቁ*

እርስዎ ለሚገኙበት የተለየ አካባቢ በ http://tinyurl.com/find-times በቀረበዉ መረጃ መሰረት፣ ከዚህ ቀጥሎ ቀረበዉን አረፍት ነገር ያሟሉ:

### *እኔ በምገኝበት አካባቢ፤የፀሀይ ግርዶሹ:*

| **ሙሉ ኑዉ** | **ሙሉ አይደለም** |
| --- | --- |

*(አንዱን ያክብቡ)*

| | |
| --- | --- |
| **እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ የፀሀይ ግርዶሹ *ሙሉ* ነዉ፤ከዚህ ቀጥሎ በቀረበዉ መረጃ ዉስጥ የሚገኙትን *መመሪያዎች* ይከተሉ**<br><br>**"እኔ በምገኝበት አካባቢ የፀሀይ ግርዶሹ *ሙሉ* ነዉ"**<br><br>**ቀጥሎ የቀረበ:** | **እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ የፀሀይ ግርዶሹ *ሙሉ አይደለም* ፤ከዚህ ቀጥሎ በቀረበዉ መረጃ ዉስጥ የሚገኙትን *መመሪያዎች* ይከተሉ**<br><br>**"እኔ በምገኝበት አካባቢ የፀሀይ ግርዶሹ *ሙሉ አይደለም* "**<br><br>**ቀጥሎ የቀረበ:** |

*© 2014-2017*
*Eclipse2017.org, inc.*

## ** እኔ በምገኝበት አካባቢ ላይ የፀሀይ ግርዶሹ *ሙሉ* ነዉ **

እርስዎ በምልዑነት አቅጣጫዉ ላይ ይገኛሉ፣እናም ያልተለመደ እና አስደናቂ ክስተትን ይመለከታሉ! እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ ላይ የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ የሚሆንበትን ጊዜ ለይቶ ማወቅ መቻል ለእርስዎ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነዉ።።ይህንንም ለማድረግ እርስዎ ከታች የመዘገቡዋቸዉን ጊዜዎች እንደማስታወሻ በመጠቀም፣ እና ከዚህም በተጨማሪ የፀሀይ ክብ በምልዑነት ወቅት ምንም አይነት ብሩህ ክፍል ስለማይኖረዉ ይህም የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ የሚሆንበትን ጊዜ ማወቅ ያስችሎታል።።

1) እርስዎ ለሚገኙበት የተለየ አካባቢ በ http://tinyurl.com/find-times በቀረበዉ መረጃ መሰረት፣ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት እያንዳንዱ የፀሀይ ግርዶሽ ክስተቶች የሚታዩበትን ግምታዊ ሰዓቶች ይጻፉ(ለእርስዎ የጊዜ ክልል ሰዓቶችን ማስተካከሎን ያረጋግጡ!):

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ከ ሲ1 በፊት** | * ምንም የፀሀይ ግርዶሽ የለም * | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ |
| **ሲ1** | **የከፊል ደረጃ የሚጀምርበት ጊዜ:** | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ |
| **ሲ2** | **ሙሉ ደረጃ የሚጀምርበት ጊዜ:** | |  |  | **ከ ሲ2 በኋላ፣** በአይንዎት መመልከት ይችላሉ |
| **መካከለኛ-የፀሀይ ግርዶሽ** | **የሚከሰትበት ጊዜ:** | |  |  | **በአይንዎት መመልከት ይችላሉ!** |
| **ሲ3** | **ሙሉ ደረጃ የሚያበቃበት ጊዜ:** | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን በድጋሚ መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ |
| **ሲ4** | **የከፊል ደረጃ የሚያበቃበት ጊዜ:** | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ |
| **ከ ሲ4 በኋላ** | * ምንም የፀሀይ ግርዶሽ የለም * | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ |

2) ምንም እንኳን እርስዎ በምልዑነት አቅጣጫ ዉስጥ ቢገኙም፣የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ በማይሆንባቸዉ ወቅቶች ማለትም ከ ሲ2 በፊት ወይም ከ ሲ3 በኋላ የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ አስፈላጊ ነዉ።።

© 2014-2017
Eclipse2017.org, inc.

3) ፀሀይን በአይንዎት(የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ሳይጠቀሙ) መመልከት የሚችሉባቸዉ ብቸኛ ሁኔታዎች :

   ሀ. እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ ላይ የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ የሚሆን ከሆነ(እርስዎ "በአቅጣጫዉ ዉስጥ" ከሆኑ)፣እና
   ለ. በምሉዕነት ጊዜዎች(እርስዎ ከላይ በመዘገቡዎቸዉ ጊዜዎች በግምት ከ ሲ2 እስከ ሲ3 የጊዜ ወቅቶች)፣እና
   ሐ. **የፀሀይ ብሩህ ክብ በጨረቃ ሙሉ በሙሉ በሚጋረድበት ጊዜያቶች**፡፡

ምሉዕነት የሚከሰትበት ትክክለኛ ጊዜዎች እርስዎ እንደሚገኙበት አካባቢ በከፍተኛ ሁኔታ ልዩነት ሊኖራቸዉ ይችላል፣ እናም ጊዜዎቹን አስቀድመዉ መለየት እና መመዝገብዎ አስፈላጊ ነዉ፡፡እርስዎ ከላይ የመዘገብዎቸዉ ጊዜዎች ግምታዊ ናቸዉ!

4) በድጋሚ፣ከላይ በተቀመጠዉ ዝርዝር ላይ የተጠቀሱት፣ወይም ከሌላ የዉጪ ምንጭ የተገኙ ጊዜዎች ግምት ዉስጥ ሳይገቡ፣**ከፀሀይ ብሩህ ክብ የትኛዉም ክፍል በሚታይበት ወቅቶች ሁልጊዜም ቢሆን ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡**

5) እነዚህ መመሪያዎች ግንዛቤን ለመፍጠር በሚረዱ ስዕላዊ የሆኑ ደጋፊ ማብራሪያዎች የሚታገዙ ናቸዉ፡፡

---

***እርስዎ የሚከተሉትን መግለጫዎች ማንበብ፣መረዳት እና መተግበርዎ አስፈላጊ ነዉ፡***

## የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ደህንነቴ ተጠብቆ እንድችል፣የመሳሪያዉን አጠቃቀም የሚመለከቱ ሁሉንም መመሪያዎች መከተል አስፈላጊ ነዉ፡፡

# ከፀሀይ ብሩህ ክብ የትኛዉም ክፍል በሚታይበት ወቅት፣ ፀሀይን ስመለከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡

## **እኔ በምገኝበት አካባቢ ላይ የፀሀይ ግርዶሹ *ሙሉ አይደለም* **

እርስዎ በምሉዕነት አቅጣጫዉ ላይ አይገኙም፣እናም የሙሉ ፀሀይ ግርዶሽን ዉበት ለመመልከት አይችሉም፡፡(ይህን አስደናቂ ሁኔታ ለመጋራት እንዲችሉ በምሉዕነት አቅጣጫ ዉስጥ እንዲገኙ አጥብቀን እንመክርዎታለን!)፡፡

1) እርስዎ ለሚገኙበት የተለየ አካባቢ በ http://tinyurl.com/find-times በቀረበዉ መረጃ መሰረት፣ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት እያንዳንዱ የፀሀይ ግርዶሽ ክስተቶች የሚታዩበትን ግምታዊ ሰዓቶች ይጻፉ(ለእርስዎ የጊዜ ክልል ሰዓቶችን ማስተካከሎን ያረጋግጡ!):

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| *ከ ሲ1 በፊት* | * ምንም የፀሀይ ግርዶሽ የለም * | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ. |
| *ሲ1* | **የከፊል ደረጃ የሚጀምርበት ጊዜ:** | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ. |
| *መካከለኛ-የፀሀይ ግርዶሽ* | **የሚከሰትበት ጊዜ:** | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ. |
| *ሲ4* | **የከፊል ደረጃ የሚያበቃበት ጊዜ:** | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ. |
| *ከ ሲ4 በኋላ* | * ምንም የፀሀይ ግርዶሽ የለም * | |  |  | የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀምዎ **አስፈላጊ** ነዉ. |

*(የ ሲ2 እና ሲ3 የጊዜ ክልሎች እንዳልተጠቀሱ ያስተዉሉ፣ምክንያቱም እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ ላይ የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ አይደለም!)*

2) **እርስዎ በሚገኙበት አካባቢ ላይ የፀሀይ ግርዶሹ ሙሉ ስለማይሆን፣ ፀሀይን ለመመልከት የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ሁልጊዜም መጠቀምዎ አስፈላጊ ነዉ፡፡** በድጋሚ፣ ወደ ምሉዕነት አቅጣጫዉ እንዲጓዙ እንመክርዎታለን፡፡የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ወደ ሚጓዙበት ቦታ ይዘዉት መሄድዎን ያረጋግጡ፣ይህም የፀሀይ ግርዶሹን የከፊል ደረጃ ደህንነቶ በተጠበቀ መልኩ ለመከታተል ያስችሎታል!

3) እነዚህ መመሪያዎች ግንዛቤን ለመፍጠር በሚረዱ ስዕላዊ የሆኑ ደጋፊ ማብራሪያዎች የሚታገዙ ናቸዉ፡፡

---

***እርስዎ የሚከተሉትን መግለጫዎች ማንበብ፣መረዳት እና መተግበርዎ አስፈላጊ ነዉ:***

## **የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን ደህንነቱ ተጠብቆ እንድችል፣የመሳሪያዉን አጠቃቀም የሚመለከቱ ሁሉንም መመሪያዎች መከተል አስፈላጊ ነዉ፡፡**

# **ፀሀይን ስመለከት ሁልጊዜም ቢሆን የፀሀይ መመልከቻ መሳሪያዉን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡**

*© 2014-2017*
*Eclipse2017.org, inc.*